الطريق إلى السعادة
The Path to Happiness
https://www.path-2-happiness.com/am




# የሰው ልጅ ሃይማኖት ያስፈልገዋል?

## ማውጫ

የሰው ልጅ ሃይማኖት ያስፈልገዋል?

ሃማኖት የግድ ነውን?
ሃይማኖት ለሕብረተሰቦች ያለው አስፈላጊነት
የእውነተኛ ሃይማኖት መመዘኛዎች
የሚያስፈልገን ሃይማኖት የቱ ነው?!

# የሰው ልጅ ሃይማኖት ያስፈልገዋል?

## ሃማኖት የግድ ነውን?

የሰው ልጅ በምንም ዓይነት ያለ ሃይማኖት መኖር አይችልም።


የሰው ልጅ በተፈጥሮው ከሕብረተሰቡ ተነጥሎ ለብቻው መኖር የማይችል ማሕበራዊ ፍጠር እንደሆነ ሁሉ፣በተፈጥሮው ያለ ሃይማኖት ትክክለኛ የሆነ ጤናማ ሕይወት መኖር የማይችል ፍጡር ነው። ስለዚህም ሃይማኖተኝነት ለሰው ልጅ ተፈጥሯዊ የሆነ ባሕርይ ነው።

### ጠንካራው ውጤት

‹‹እምነት ከሁሉም ጠንካራውና በጣም ውዱ የሳይንሳዊ ምርምሮች ውጤት ነው››

**አይንሽታይን**

**የፊዚክስ ሊቅ**



የሰው ልጅ ሲጨነቅና መከራ ሲገጥመው ወደ አላህ (ሱ.ወ.) ተመልሶ የሚማጸነው ከመሆኑ የበለጠ ማስረጃ የለም።አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴿٦٥﴾}[العنكبوت: ٦٥]

‹‹በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም፣አላህን፣መግገዛትን ለርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ያጠሩታል፤ወደ የብስ (በማውጣት) ባዳናቸው ጊዜም ወዲያውኑ እነርሱ (ጣዖትን) ጋራሉ።››[አል ዐንከቡት፡14]

አንድን ዕቃ የሚሰራ ወገን ዕቃውንና የሚያስፈልጉትን ነገሮች ከማንም በላይ እንደሚያውቅ ሁሉ፣ፈጣሪ አምላክ ስለ ፍጡራኑና አስፈላጊያቸው ስለሆኑ ነገሮች ሁሉ ከማንም በላይ ያውቃል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾}[الملك: ١٤]

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ አዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን፡፡››[አልሙልክ፡14]

ፈጣሪ ርህሩህ መሐሪና ቸር በመሆኑ፣የሰዎች መንፈስ ሕያው ሆኖ ሕይወታቸውን በሥርዓት ይመሩ ዘንድ ጃይማኖትን ደንግጎላቸዋል።አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱسْتَجِيبُوا۟ لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمْ لِمَا يُحْيِيكُمْ}[الأنفال: ٢٤]

‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! (መልክተኛው ሕያው ወደሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ፣ለአላህና ለመልክተኛው ታዘዙ፤)››[አል አንፋል፡24]

በመሆኑም ተፈጥሮን በመጻረር የአላህን ሕልውና እንክዳለን የሚሉ ወገኖች እንኳ በውስጣቸው ውሸታቸውንና ክህደታቸውን ያውቃሉ። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَجَحَدُوا۟ بِهَا وَٱسْتَيْقَنَتْهَآ أَنفُسُهُمْ ظُلْمًا وَعُلُوًّا ۚ فَٱنظُرْ كَيْفَ كَانَ عَـٰقِبَةُ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿١٤﴾}[النمل: ١٤]

‹‹ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲኾኑ ለበደልና ለኩራት በርሷ ካዱ፤የአመጸኞችም ፍጻሜ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከት፡፡››[አልነምል፡14]

በጭንቅና በመከራ ሰዓት አስገዳጅ ሁኔታ ሲያጋጥመው ይህን በግልጽ ያያል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلْ أَرَءَيْتَكُمْ إِنْ أَتَىٰكُمْ عَذَابُ ٱللَّهِ أَوْ أَتَتْكُمُ ٱلسَّاعَةُ أَغَيْرَ ٱللَّهِ تَدْعُونَ إِن كُنتُمْ صَـٰدِقِينَ ﴿٤٠﴾ بَلْ إِيَّاهُ تَدْعُونَ فَيَكْشِفُ مَا تَدْعُونَ إِلَيْهِ إِن شَآءَ وَتَنسَوْنَ مَا تُشْرِكُونَ ﴿٤١﴾}[الأنعام: ٤١- ٤٢]

### ሃይማኖተኛና ሕሙማን



‹‹ሰዎች ስለ ሳይንስና ሃይማኖት መራራቅ እንጂ ሌላ ነገር የማያወሩበት ጊዜ ትዝ ይለኛል። ይህ ክርክር ግን ላይመለስ አብቅቷል። በጣም አዲስ የሆነው የስነልቦና ሕክምና ሳይንስ በሃይማኖት መርህ ያበስራል፤ለምን?! የስነልቦና ሐኪሞች ጠንካራ እምነት፣ሃይማኖትና ጸሎትን አጥብቆ መያዝ፣ጭንቀትን፣ስጋትንና ውጥረትን ለማስወገድና ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በሽታዎችን ለመፈወስ አመርቂ ውጤት እንዳላቸው ስለሚገነዘቡ ነው። ዶክተር ኤ፣ኤ፣ብሬል ‹ሃይማኖተኛ ሰው በእርግጥ በስነልቦና በሽታ ፈጽሞ አይጠቃም› እስከማለት ደርሰዋል፡፡››

**ዴል ካርኒጂ**

**አሜሪካዊ ደራሲ**

‹‹የአላህ ቅጣት ቢመጣባችሁ ወይም ሰዓቲቱ (ትንሣኤ) ብትመጣባችሁ፣ከአላህ ሌላን ትጠራላችሁን? እውነተኞች እንደ ኾናችሁ ንገሩኝ በላቸው። አይደለም እርሱን ብቻ ትጠራላችሁ፤ቢሻም ወደርሱ የምትጠሩበትን ነገር ያስወግዳል፤የምታጋሩትንም ነገር ትተዋላችሁ (በላቸው)፡፡››[አል አንዓም፡41-42]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا مَسَّ ٱلْإِنسَـٰنَ ضُرٌّ دَعَا رَبَّهُۥ مُنِيبًا إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَا خَوَّلَهُۥ نِعْمَةً مِّنْهُ نَسِىَ مَا كَانَ يَدْعُوٓا۟ إِلَيْهِ مِن قَبْلُ وَجَعَلَ لِلَّهِ أَندَادًا لِّيُضِلَّ عَن سَبِيلِهِۦ ۚ قُلْ تَمَتَّعْ بِكُفْرِكَ قَلِيلًا ۖ إِنَّكَ مِنْ أَصْحَـٰبِ ٱلنَّارِ ﴿٨﴾}[الزمر: ٩]

https://www.path-2-happiness.com/am



ዴል ካርኒጂ
አሜሪካዊ ደራሲ

## ጥልቅ ሁን

ፈላስፋው ፍራንሲስ ቢኮን ፦ ‹‹ጥቂቱ ፍልስፍና ሰውን ወደ ኤቲዝም ሲቀርብ፣የፍልስፍና ጥልቅ ዕውቀት ግን ወደ ሃይማኖት ይመልሰዋል›› ማለቱ በጣም ትክክል ነበር።

**‹‹ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ፣ጌታውን ወደርሱ ተመላሽ ኾኖ ይጠራል። ከዚያም ከርሱ ዘንድ ጸጋን በሰጠው ጊዜ ያንን ከዚያ በፊት ወደርሱ ይጸልይበት የነበረውን (መከራ) ይረሳል፤ከመንገዱ ለማሳሳትም ለአላህ ባላንጣዎችን ያደርጋል፤በክሕደት ጥቂትን ተጣቀም፤አንተ በእርግጥ ከእሳት ጓዶች ነህ በለው።››**[አል ዙመር፡8]

መላው የሰው ዘር አላህ በፈጠራቸው ንጹሕ ተፈጥሯቸው፣በጥቀምም ሆነ መጉዳት በእጁ የሆነውን፣ያሻውን የሚሰራና የፈለገውን የሚወስን የሆነውን አንድ አምላክ የማምለክ ባሕርይ ይዘው ተወልደዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يَمۡسَسۡكَ بِخَيۡرٖ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ١٧}[الأنعام: ١٧]

**‹‹አላህም በጉዳት ቢነካህ ለርሱ (ለጉዳቱ) ከእርሱ በቀር ሌላ አስወጋጅ የለም፤በበጎም ነገር ቢነካህ እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።››**[አል አንዓም ፡14]

በተጨማሪምአላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَّا يَفۡتَحِ ٱللَّهُ لِلنَّاسِ مِن رَّحۡمَةٖ فَلَا مُمۡسِكَ لَهَاۖ وَمَا يُمۡسِكۡ فَلَا مُرۡسِلَ لَهُۥ مِنۢ بَعۡدِهِۦ}[فاطر: ٢]

**‹‹አላህ ለሰዎች ከችሮታ የሚከፍታት ለርሷ ምንም አጋጅ የላትም፤የሚያግደውም ከርሱ በኋላ ለርሱ ምንም ለቃቂ የለም፤እርሱም አሸናፊው፣ጥበበኛው ነው።››**[ፋጢር፡2]

ሰው ሁለት ኃይሎች አሉት፤አንደኛው የዕውቀት ኃይል ሲሆን ሌላው የፍላጎት ኃይል ነው። ሁለቱን እውን ለማድረግ በሚያደርገው ጥረት መጠንም ከፈለገው ግብ ይደርሳል። የመጀመሪያውን ማለትም የዕውቀትን ኃይል በተመለከተ፣ለአላህ ለስሞቹና ለባህርያቱ፣ለትእዛዛቱና ለእገዳዎቹ ግዴታ የሆነበትን በማወቁ ረገድ በሚኖረው ዕውቀት መጠን፣በተግባራዊ ስነምግባሩና በጸባዩ፣ወደ አላህ የቀረቡ ደጋግ አገልጋዮቹን መንገድ እንዴት እንደሚከተል፣በተጓዦቹየመወጣጫደረጃዎች ላይ እንዴት ከፍ እንደሚል፣ስለ ሰው ልጅ ነፍስያ ውስጣዊ ተፈጥሮ፣ስለ ደዌዎቿና ስለ ቆሻሻዎቿ፣እንዴት ሊረታትና ሊገራት እንደሚችል፣በጠላቶቿና እርሷን ከጌታዋ በሚያግዱት ሁሉ ላይ እንዴት ድል መቀዳጀት እንደሚቻል በሚኖረው እውቀት ደረጃ፤ወደ መጠቀ መንፈሳዊ ደረጃና ወደ ላቀ መንፈሳዊ ግብ በሚያደርሰው መልኩ ራሱን ከርካሽ ቁሳዊ ፍላጎቶችና የወረዱ ስሜታዊ ዝንባሌዎች በራቀ ሁኔታ በውብ ስነምግባርና በምስጉን ባሕርያት ከማነጽና ከመግራት ጎን ለጎን . . ለአላህ የሚኖረው ተገዥነትና ተመሪነት፣አላህ ዘንድ የሚኖረው ደረጃና ስፍራም፣የወዳኛው ሕይወት ተድላና በደስታ ብቻ ሳይሆን የዚች ዓለም ተድላና ደስታውም ጭምር በዚህ መጠን ይሆናል።



### ጉልሁ እውነታ

‹‹የዶክትሬት ዲግሪ ጥናቴ በስነትምሕርትና በአገር (nation) ግንባታ ላይ ያተኮረ ሲሆን፣መሠረታዊ የእስላም ማእዘናት አገርን በማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና መንፈሳዊ ዘርፎች ዳግም ለመገንባት ትልቅ መሠረት የሚጥሉና ጠቃሚ መርህ የሚያቀርቡ መሆናቸውን ለማወቅ ችያለሁሉና።››

ዶክተር ዳግላስ
የሪጂና ከንቲባ

ይልቁንም ይህ የዕውቀት ኃይልና አቅም ከጽናትና ከቀጥተኝነት በተጨማሪ በውስጡ ባካተተው ቅን መመሪያ፣የፍላጎት ኃይል መጋቢና ስንቅ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسۡتَجِيبُواْ لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمۡ لِمَا يُحۡيِيكُمۡ}[الأنفال: ٢٤]

**‹‹እላንተ ያመናችሁ ሆይ! (መልክተኛው) ሕያው ወደሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ፣ለአላህና ለመልክተኛው ታዘዙ፤››**[አል አንፋል፡24]

ይኸውና የኤቲዝም ጎራዎች የመንፈስ እርካታን ማስገኘት ቀርቶ የአካልን እርካታ ማስፈን ስለተሳናቸው ክስረታቸውን እያወጁ ነው። ያሻቸውን ያህል ብልጭልጭ የማታለያ ቃላቶቻቸውን እርስበርሳቸው ቢለዋጡና አሰማምረው ቢነዙ እውነተኛውን ደስተኙነት ለሰውልጆች ለማቅረብ ሳይችሉ መክነዋል።

የሰው ልጅ በአደጋና በመከራ ወቅት ወደማነው የሚማጸነውና የሚወተውተው?! ወደ ብርቱው ማእዘን ነው የሚጠጋው፤ኃይልና ተስፋ፣ክጀላና ትዕግስት፣በጎ መተማመንና ነገሮችን ሁሉ ለርሱ መስጠት ወዳለበት ወደ ኃያሉ አላህ ነው የሚሸሸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ٢٨}[الرعد: ٢٨]

**‹‹(እነሱም)እነዚያያመኑ፣ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት**



https://www.path-2-happiness.com/am



## ሃይማኖተኝነት ለበሽታዎች ፈውስ ነው

‹‹ጠንካራ እምነትና ሃይማኖትን አጥብቆ መያዝ፣ጭንቀትን፣ስጋትንና ውጥረትን ለማስወገድና እነዚህን በሽታዎች ለመፈወስ አመርቂ ውጤት እንዳላቸው የስነልቦና ሐኪሞች ይገነዘባሉ::››

**ዴል ካርኒጂ**

**አሜሪካዊ ደራሲ**


## ራስህን በራስህ ፈውስ

‹‹ለመንፈስ ጭንቀት ታላቁ ፈውስ በአላህ ማመን ነው::››

**ዊልያም ጀምስ**

**አሜሪካዊ የስነልቦና ሊቅ**





## ሁለቱ ይለያያሉ

‹‹ቁሳዊነት ሁሌም የሚያረጋግጠው በእንስሳና በሰው መካከል የጋራ የሆነውን ነገር ሲሆን . . ሃይማኖት ግን በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ያረጋግጣል::››

**ዐሊ. ዐዘት ቢጎቢች**

**የቀድሞ የቦስኒያ ሄርዝጎቪኒያ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

የሚረኩ ናቸው፤ንቁ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ::››[አል ረዕድ፡28]

በግፍና በጭቆና እሳት ተለብልቦ ምሬት ሲሰማው ይህ ዩኒቨርስ ፈጣሪ ጌታ እንዳለው፣ቆይቶም ቢሆን ለጭቁን ተጎጂው ረድኤቱ እንደሚመጣ፣እያንዳንዱ ሰው እንደሥራው ዋጋውን የሚያገኝበትና በጎ የሠራም ሆነ ክፉ የሠራው ፍርዱን የሚያይበት የትንሣኤ ቀን ስለመኖሩ እርግጠኛ ይሆናል:: በዚህም በአላህ (ሱ.ወ.) ላይ በሚኖረው መተማመንና እርግጠኝነት ልቡ ይረካል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَمَنِ ٱتَّبَعَ رِضۡوَٰنَ ٱللَّهِ كَمَنۢ بَآءَ بِسَخَطٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَمَأۡوَىٰهُ جَهَنَّمُۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ١٦٢} [آل عمران: ١٦٢]

‹‹የአላህን ውዴታ የተከተለ ሰው፣ከአላህ በኾነ ቁጣ እንደ ተመለሰና መኖሪያው ገሀነም እንደ ኾነ ሰው ነውን? መመለሻውም ምን ይከፋ!››[ኣሊ. ዒምራን፡162]

በተቃራኒው ደግሞ አላህን (ሱ.ወ.) ማወቅና በርሱ ማመንን ያጣ ሰው ሁሉንም ኃይል ያጣ፣የመንፈስ እርካታና ውስጣዊ መረጋጋትን፣ደስተኝነትም ተነፍጎ በጭንቀት በውጥረትና በሀዘን ማእበል ውስጥ የሚኖር ሰው ነው:: የተረጋጋ አእምሮም ሆነ ውስጣዊ ሰላም የሌለው ሲሆን፣ብቸኛ ግቡ ሥጋዊ መደሰቻንና ስሜታዊ ፍላጎቶችን ለማርካት ገንዘብ ማሳደድ ነው:: የሚኖርለት ዓላማም ሆነ የሕይወት ግብ የሌለው፣



ደስተኝነትን ፍለጋ ሲለፋና ሲባዝን የሚኖር፣የስጋዊ ፍላጎቶቹ ተገዥ ሆኖ የሚኖር በመሆኑ ከሰውነት እየወረደ ወደ እንስሳዊነት ብቻ ሳይሆን ከዚያም ወደ ከፋ ይዘቅጣል::አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَمۡ تَحۡسَبُ أَنَّ أَكۡثَرَهُمۡ يَسۡمَعُونَ أَوۡ يَعۡقِلُونَۚ إِنۡ هُمۡ إِلَّا كَٱلۡأَنۡعَٰمِ بَلۡ هُمۡ أَضَلُّ سَبِيلًا ٤٤} [الفرقان: ٤٤]

‹‹ይልቁንም አብዛኞቻቸው የሚሰሙ፣ወይም የሚያውቁ፣መኾናቸውን ታስባለህን? እነርሱ እንደ እንስሳዎች እንጂ ሌላ አይደሉም፣ከቶውንም እነሱ ይልቅ መንገድን የተሳሳቱ ናቸው::››[አል ፉርቃን፡44]


ስቃይና መከራ ስለወረረው የስነልቦና ውድመትና የውስጣዊ ጭንቀት ሰለባ ይሆናል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَنۡ أَعۡرَضَ عَن ذِكۡرِي فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةٗ ضَنكٗا وَنَحۡشُرُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ أَعۡمَىٰ ١٢٤} [طه: ١٢٤]

‹‹ከግሣጼም የዞረ ሰው፣ለርሱ ጠባብ ኑሮ አልለው፤በትንሣኤም ቀን ዕውር ኾኖ እንቀሰቅሰዋለን::››[ጣሃ፡124]

ጌታው ያወቀ፣ኃያልነቱን የተገነዘበ፣ለርሱ መፈጸም የሚገባቸውን ግዴታዎችም የተረዳ፤ሸሪዓውን በመከተል ለትእዛዛቱ ታዛዥ በመሆንና ከእገዳዎቹ በመከልከል የርሱን ውዴታ ለማግኘት የጓጓ፤ጌታው በትንሹም በትልቁም፣በግልጹና በስውሩም፣በሁሉም ጊዜና ስፍራም ለርሱ ወሳኝና የዘውትር


## ሰባኪያን ሐኪሞች




‹‹የስነልቦና ሐኪሞች አዲስ ዓይነት ሰባኪያን እንጂ ሌላ አይደሉም:: ሃይማኖትን አጥብቀን እንድንይዝ የሚጎተጉቱን የወዲያኛውን ዓለም የገሀነም ቅጣት በመስጋት ሳይሆን፣ሃይማኖትን እንድንይዝ የሚመክሩን የዚችን ዓለማዊ ሕይወት ሲኦል፣ከየጨጓራ ቁስልን፣የስነልቦና መናድንና የእብደትን ገሀነም በመስጋት ነው::››

**ሄንሪ ፎርድ**

**የአሜሪካው ፎርድ ኩባንያ መስራች**





https://www.path-2-happiness.com/am


https://www.path-2-happiness.com/am

አስፈላጊው መሆኑን ያወቀ ሰው ይህን ሁሉ ከማያውቀው ሰው የተለየ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلْفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِ ۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلْغَنِىُّ ٱلْحَمِيدُ ﴿١٥﴾} [فاطر: ١٥]

‹‹እላንተ ሰዎች ሆይ! እናንተ (ሁል ጊዜ) ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ፤አላህም እርሱ ተብቃቂው ምስጉኑ ነው።››[ፋጢር፡15]

ልቡ በጥርጣሬና በግራመጋባት ተሞልቶ እርግጠኝነትን ማጣትና ባዶ ግምቶች ወደ መከፋትና ተስፋ መቁረጥ ጨለማ የወሰዱት ሰው፣ዓለማዊ መደሰቻዎችንና ጊዜያዊ ማርኪያዎችን ቢያገኝም፣ከፍተኛ ሹመትና ማእረግ ማግኘት ቢሳካለትም እንኳ እውነተኛ ደስተኝነትንና ውስጣዊ እርካታን የማግኘት ጥረቱ ከንቱ ይሆናል። አላህን ለማግኘት ያልታደለ ምን አግኝቶ?! አላህን ያገኘ ምን አጥቶ?!



## ሃይማኖት ሕይወት ነው

‹‹ሃይማኖት ወሳኝ ከሆኑ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ተሰጥኦዎች አንዱ ነው። የሃይማኖት እጦት አንድን ሰው፣ምኑም የራሱ ካልሆነ ገበታ ላይ ሃይማኖታዊ ማጽናኛ ፍለጋ ለመሄድ ወደሚያስገድደው የተስፋ መቁረጥና የመንፈስ ዝቅጠት ሁኔታ ያስገባዋል።››

**አርኖልድ ቱዌይንቢ**

**እንግሊዛዊ ታሪክ ጸሐፊ**



## ዘመነ ጭንቀት

‹‹ዛሬ የምንኖረው በዘመነ ጭንቀት ነው፤የሳይንስና የቴክኖሎጂ ስኬቶች ለሰው ልጅ እድገትና ብልጽግናን መጨመራቸው እሙን። ይሁን እንጂ ደስተኝነትንና ውስጣዊ እርካታን አልጨመሩለትም። በተጻራሪው ጭንቀትን፣ተስፋ መቁረጥንና በሕይወቱ ውስጥ ያለውን ውብ ትርጉም ያሳጡትን የስነልቦና በሽታዎችን ነው የጨመሩለት።››

**ሬይኔ ዶሎ**

**የኖቤል ሽልማት ተሸላሚ ደራሲ**





# ሃይማኖት ለሕብረተሰቦች ያለው አስፈላጊነት

ሃይማኖት ለግለሰብ ወሳኝ አስፈላጊ ከሆነ ዘንዳ ለሕብረተሰቦች የሚኖረው አስፈላጊነት ይበልጥ የጸና ይሆናል። የሰው ልጆች ሕይወት በመካከላቸው በሚኖረው በበጎ ነገሮች ላይ የመረዳዳትና የመተባበር መሰረት ላይ እንጂ የማይታነጽ በመሆኑ፣ሃይማኖት ለአንድ ሕብረተሰብ የመከላከያ ጋሻ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَتَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلْبِرِّ وَٱلتَّقْوَىٰ ۖ وَلَا تَعَاوَنُوا۟ عَلَى ٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ} [المائدة: ٢]

‹‹በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፤ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ።››[አል ማእዳህ፡2]

ይህ ተራድኦና ትብብር ሊኖር የሚችለው ደግሞ ግንኙነቶቻቸውን በሚያደራጅ፣ግዴታዎቻቸውን በሚወስንና ለመብቶቻቸው ዋስትና በሚሰጥ ሥርዓት አማካይነት ብቻ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓትም የግዴታ ውስጠ ዐዋቂና ጥበበ ረቂቅ በመሆኑ ከማንም በላይ ለፈጠራቸው ፍጡራን የሚበጀውን ከሚያውቀው ኃያል አምላክ ዘንድ የመጣ መሆን ይኖርበታል።

{أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾} [الملك: ١٤]

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ አዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ)




## አፍ አውጥቶ የሚናገር ማስረጃ

‹‹የምንወደው ማንኛውም ነገር መመንመኑ፣አእምሮን ሳይንስንና እንዱስትሪን የመጠቀም ነጻነትም ሊከሽፍ ይችላል። ሃይማኖተኝነት ግን ፈጽሞ ሊከስም አይችልም። ይልቁንም ሰውን በምድራዊ ሕይወት ወራዳ ጠባብ መተላለፊያዎች ውስጥ ብቻ ወስኖ ለማስቀረት የሚፈልገው የቁሳዊነት አመለካካት ውድቅ መኾኑን ጮሆ የሚናገር ማስረጃ እንደሆነ ይቀጥላል።››

**አርነስት ሬናን**

**ፈረንሳዊ ታሪክ ጸሐፊ**



**ፊሊፐ ሃቴይ**
**ሊባኖሳዊ ታሪክ ጸሐፊ**

## እውነተኛው ሕግ

‹‹እስላማዊው ሽሪዓ (ሕግ) ሃይማኖታዊውንና ዓለማዊውን ለያይቶ የማይመለከት ሲሆን፣የሰው ልጅ ከአላህ ጋር ያሚኖሩትን ግንኙነቶች፣ለአላህ ያለበትን ግዴታዎች በመደንገግ ያደራጃል። የሰው ልጅ ከመሰል ሰብአዊ ወንድሙ ጋር የሚኖሩትን ግንኙነቶችም እንዲሁ ይደነግጋል። ከሃማኖታዊ ዓለማዊና ሌሎችም ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ሁሉም የአላህ ትእዛዛትና እገዳዎች ቁርኣን ውስጥ ሰፍረዋል። ቁርኣን ውስጥ ከስድስት ሺ አንቀጾች በላይ ሲኖሩ አንድ ሺ ያህሎቹ ድንጋጌዎችን የሚመለከቱ ናቸው።››

https://www.path-2-happiness.com/am

### ለስሜታዊ ዝንባሌዎች ቦታ የሌለው ሃይማኖት

‹‹ሙሐመድ በመዲና ላገኙት ሞቅ ያለ አቀባበል ምክንያት ከሆኑት ውስጥ፣ለሊሂቃኑ መደብ የመዲና ነዋሪዎች ወደ እስላም መግባት የማህበረሰቡ ችግር ሆኖ ለቆየው ለዚያ ሥርዓተ አልበኝነት መፍትሔ ሆኖ መታየቱ አንዱ ነው:: ይህም በእስላም ውስጥ ባገኙት ጥብቅ የአነዋነዋር ሥርዓትና የሰዎችን ልቅና አፈንጋጭ ስሜታዊ ዝንባሌዎች ከግለሰባዊ ዝንባሌዎች በላይ ከሆነው ሥልጣን ለተደነገጉ ሕጎች ተገዥ በማድረግ አቅሙ ነው::››

ቶማስ አርኖልድ
እንግሊዛዊ ኦሪየንታሊስት


### አእምሯችሁ የት ሄደ?!

‹‹በአላህ መኖር ለምንድነው የምትጠራጠሩት?! እርሱ ባይኖር ኖሮ ባቤቴ ክህደት በፈጸመችብኝ፣አገልጋዬም በሰረቀን ነበር::››

ቮልተር

ፈረንሳዊ ፈላስፋ





አያውቅምን::››[አል ሙልክ:14]

የሰው ልጆች ከሃይማኖት ከሕግጋቱና ከሥርዓቱ ባፈነገጡ ልክ፣በጥርጣሬ፣በጥመት፣በብክነት፣በመባዘን፣ግራ በመጋባት፣በመናጢነትና በመላየለሽነት ጨለማ ውስጥ ይዋጣሉ::

በሕብረተሰቡ ውስጥ አንድነትን ሰላምንና መረጋጋትን ለማስፈን፣ሕግና ሥርዓትን ለማስከበር ከሃይማኖት ኃይል ጋር የሚነጻጸር ወይም የሚቀርበው ምንም ዓይነት ሌላ ኃይል በዓለም ላይ የለም:: የዚህ ምስጢር ደግሞ የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎቹና ድርጊቶቹ በራሱ ምርጫ የሚፈጸሙና በማይታይና በማይጨበጥ ነገር የሚመሩ በመሆናቸው ከተቀሩት ሕያው ፍጥረታት ሁሉ የተለየ ነው:: እንቅስቃሴዎቹና ድርጊቶቹ የሚመሩት መንፈሱን በሚያጠራ፣ጸባይና ስነምግባሩን በሚገራ፣ግልጹን አካላዊ እንቅስቃሴውን እንደሚቆጣጠረው ሁሉ ስውሩን ውስጣዊ ሕሊናዊ ሁኔታውንም በሚቆጣጠረው ሃይማኖታዊ እምነት ነው::

{وَإِن تَجۡهَرۡ بِٱلۡقَوۡلِ فَإِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلسِّرَّ وَأَخۡفَى ٧}[طه: ٧]

‹‹በንግግር ብትጮኽ፣(አላህ ከጩኸቱ የተብቃቃ ነው)፤እርሱ ምስጢርን፣በጣም የተደበቀንም ያውቃልና::››[ጣሃ:7]


የሰው ልጅ ትክክለኛም ይሁን የተሳሳተ የሚመራው ሁሌም በእምነት (በዐቂዳ) ነው:: ዐቂዳውጥሩና ትክክለኛ ከሆነ ነገሩ ሁሉ መልካም ይሆንለታል፤መጥፎና የተሳሳተ ከሆነ ደግሞ ነገሩ ሁሉ የተበላሸ ይሆናል::

በመሆኑም ሃይማኖት በሰዎች መካከል በይነሰባዊ ግንኙነቶች በፍትሕና ርትእ መሠረቶች ላይ የታነጹ እንዲሆኑ የሚያደርግ አስተማማኝ ዋስትና ነው::



በዚህ ምክንያትም ሃይማኖት ማሕበረሰባዊ ግዴታ በመሆኑ በሕዝቦች መካከል የሚይዘው ስፍራ ልብ በሰው አካል ውስጥ የሚይዘው ስፍራ መሆኑ አስደናቂ አይሆንም::

ሃይማኖት በአጠቃላይ መልኩ ይህን የመሰለ ደረጃ የያዘ ሲሆን፣ዛሬ በዓለም ላይ የምናስተውለው ግን የተለያዩ ሃይማኖቶች፣እምነቶችና ጎራዎች መኖራቸውን ነው:: የእያንዳንዱ እምነትና ጎራ ተከታዮችም በእምነታቸው ደስተኞች ሆነው የሙጥኝ መያዛቸውን እንመለከታለን:: ታድያ የሰው ልጅ የሚጓጓለትን ግብ እውን የሚያደርግለት እውነተኛው ሃይማኖት የትኛው ይሆን?! የእውነተኛ ሃይማኖት መመዘኛዎችስ ምንድናቸው?!



## የእውነተኛ ሃይማኖት መመዘኛዎች

የአንድ እምነት ተከታይ የሆነ ሰው የርሱ እምነት ከተቀሩት እምነቶች ሁሉ ትክክለኛውና ዓይነተኛው እምነት ስለመሆኑ ሁሌም ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሆኖ እናገኘዋለን:: የያንዳንዱ እምነት ተከታይም ይህን የሚተነትንበት የራሱ የተለየ መንገድ አለው:: የብልሹ ሰው ሠራሽ ወይም የተዛቡ ሃይማኖቶች ተከታዮች የእምነታቸውን ትክክለኛነት የሚተነትኑት አባቶቻቸው ይህንኑ ሲከተሉ ያገኟቸው መሆኑንና የነሱን ዱካ የሚከተሉ መሆናቸውን በመግለጽ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَكَذَٰلِكَ مَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ فِي قَرۡيَةٖ مِّن نَّذِيرٍ إِلَّا قَالَ مُتۡرَفُوهَآ إِنَّا وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا عَلَىٰٓ أُمَّةٖ وَإِنَّا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم مُّقۡتَدُونَ ٢٣ ۞ قَٰلَ أَوَلَوۡ جِئۡتُكُم بِأَهۡدَىٰ مِمَّا وَجَدتُّمۡ عَلَيۡهِ ءَابَآءَكُمۡۖ قَالُوٓاْ إِنَّا بِمَآ أُرۡسِلۡتُم بِهِۦ كَٰفِرُونَ ٢٤}[الزخرف: ٢٣-٢٤]

‹‹(ነገሩ) እንደዚሁም ነው፤ከበፊትህ በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ አስፈራሪን አልላክንም፣ቅምጥሎችዋ፣እኛ አባቶቻችንን በሃይማኖት ላይ አገኘን፤እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተከታዮች ነን ያሉ ቢኾኑ እንጅ:: (አስፈራሪው) አባቶቻችሁን በርሱ ላይ ከአገኛችሁበት ይበልጥ ቀጥተኛን (ሃይማኖት) ባመጣላችሁም? አላቸው፤እኛ በርሱ በተላካችሁበት ነገር ከሓዲዎች ነን አሉ::››[አል ዙኽሩፍ:23-24]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّبِعُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُواْ بَلۡ نَتَّبِعُ مَآ أَلۡفَيۡنَا عَلَيۡهِ ءَابَآءَنَآۚ أَوَلَوۡ كَانَ ءَابَآؤُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ شَيۡـٔٗا وَلَا يَهۡتَدُونَ ١٧٠ وَمَثَلُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ كَمَثَلِ ٱلَّذِي يَنۡعِقُ بِمَا لَا يَسۡمَعُ إِلَّا دُعَآءٗ وَنِدَآءٗۚ صُمُّۢ بُكۡمٌ عُمۡيٞ فَهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ ١٧١}[البقرة: ١٧٠-١٧١]



https://www.path-2-happiness.com/am

‹‹ለነርሱም አላህ ያወረደውን ተከተሉ በተባሉ ጊዜ፣አይደለም አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር እንከተላለን ይላሉ፤አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና (ወደ አውነት) የማይመሩም ቢኾኑ (ይከተሉዋቸዋልን?) የነዚያም የካዱት(ና ወደ ቅን መንገድ የሚጠራቸው ሰው) ምሳሌ እንደዚያ ድምጽንና ጥሪን በስተቀር ሌላን በማይሰማ (እንስሳ) ላይ እንደሚጮኽ ብጤ ነው፤(እነርሱ) ደንቆሮዎች፣ዲዳዎች፣ዕውሮች ናቸው፤ስለዚህ እነርሱ አያውቁም::››[አል በቀራህ:170-171]

አቋማቸው አእምሮን ማሰራት ወይም ማሰብና ማስተዋል ሳያስፈልግ በአስጠሊው ጭፍን ተከታይነት ላይ የሚሞረኮዝ ነው:: ወይም በተሳሰቱ፣በተጣመሙና እርስ በርሳቸው የሚጋጩ፣ትክክለኛ ስለ መሆናቸው ማስረጃም ሆነ ማረጋገጫ በሌላቸው ዘገባዎች ላይ ይሞረኮዛሉ:: በእርግጥ እንዲህ ያሉ ነገሮችን ሃይማኖቶችንና እምነቶችን በሚመለከት በማስረጃነት ማቅረብ ስሕተት ነው::

እውነት የማከፋፈል አንድ ብቻ በመሆኑ እነዚያ እምነቶች ሁሉ በአንድ ጊዜ ትክክለኞች ይሆናሉ ማለት ፈጽሞ የማይቻል ነው፤አሊያ እውነት እርስ በርሱ የሚጻረር ሊሆን ነው፤ይህ ደግሞ ጤናማ አእምሮ የማይቀበለው ነገር ነው::

{وَلَوۡ كَانَ مِنۡ عِندِ غَيۡرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ ٱخۡتِلَٰفٗا كَثِيرٗا ﴿٨٢﴾}[النساء: ٨٢]

‹‹ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር::››[አል ኒሳእ:82]

ታድያ እውነተኛው ሃይማኖት ምንድነው? ከነዚህ እምነቶች መካከል አንዱ ብቻ እውነተኛው እምነት ነው መመዘኛውን የማያሟሉ የተቀሩት እምነቶች ብልሹና የተሳሳቱ ናቸው ለማለት የሚያስችሉን መመዘኛዎች የትኞቹ ናቸው?!

መመዘኛዎቹ የሚከተሉት ናቸው፦

አንደኛ ፦ የሃይማኖቱ ምንጭና መገኛ መለኮታዊነት ማለትም ከአላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ የተላለፈ መሆን ነው:: ይህም ለአገልጋዮቹ ያደርስ ዘንድ በመልኣክ አማካይነት ከአላህ መልክተኞች ወደ አንዱ የተላለፈ መሆን ማለት ነው:: እውነተኛው ሃይማኖትም ይህን ዩኒቨርስ ከፈጠረው አላህ (ሱ.ወ.) የተላለፈ ሃማኖት ሲሆን፣ባስተላለፈላቸው ሃይማኖት መሠረት ፍጡራንን በትንሣኤው ቀን የሚጠይቃቸውና የሚመረምራቸው አላህ (ሱ.ወ.) ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

## አንድ ብቻ ነው

‹‹በእስላም ውስጥ መሰረታዊው አውነታ የአላህ አንድነት ነው:: አላህ አንድ ነው፣ሙሐመድ የአላህ መልክተኛ ነው:: ማጋራት ግን ወደ ጎን ተሽቀንጥሯል፤አባትም ሆነ ልጅ የለም፤ቅዱስ በሆነው ነገርና በዓለማዊው ነገር መካከል፣በምሥራቃዊውም ሆነ በምዕራባዊው መካከልም ልዩነት የለም:: ያለው አንድ ዓለምና አንድ ሃይማኖት ነው::››

**ሚካኤል ሄምዝ**
**እንግሊዛዊ ጸሐፊ**



{إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَٰرُونَ وَسُلَيۡمَٰنَۚ وَءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ زَبُورٗا ﴿١٦٣﴾ وَرُسُلٗا قَدۡ قَصَصۡنَٰهُمۡ عَلَيۡكَ مِن قَبۡلُ وَرُسُلٗا لَّمۡ نَقۡصُصۡهُمۡ عَلَيۡكَۚ وَكَلَّمَ ٱللَّهُ مُوسَىٰ تَكۡلِيمٗا ﴿١٦٤﴾ رُّسُلٗا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةُۢ بَعۡدَ ٱلرُّسُلِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمٗا ﴿١٦٥﴾}[النساء: ١٦٣-١٦٥]

‹‹እኛ ወደ ኑሕና ከርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነቢያት እንዳወረድን፣ወደ አንተም አወረድን፤ወደ ኢብራሂምም፣ወደ እስማዒልም፣ወደ እስሓቅም፣ወደ የዕቁብም፣ወደ ነገዶቹም፣ወደ ዒሳም፣ወደ አዩብም፣ወደ ዩኑስም፣ወደ ሃሩንና ወደ ሱለይማንም አወረድን፤ለዳውድም ዘቡርን ሰጠነው:: ከዚህም በፊት በአንተ ላይ በእርግጥ የተረክናቸውን መልክተኞች፣ባንተ ላይም ያልተረክናቸውን መልክተኞች (እንደላክን፣ላክንህ):: አላህም ሙሳን ማነጋገርን አነጋገረው::››[አል ኒሳእ:163-165]

በዚህ መሠረት ከአላህ ጋር ሳይሆን ከራሱ ጋር የተዛመደ ሃይማኖት ይዞ የሚመጣ ማንኛውም ሰው ሃይማኖቱ የግድ ውድቅ የሆነ ሃይማኖት ነው:: ሰዎች የሚፈጥሩትና እየጨመሩበትና እየቀነሱበት የሚያሻሽሉት ሃይማኖትም እንዲሁ ውድቅና ተቀባይነት የለውም:: ሃይማኖትን የሚያሻስሉትና የሚለዋውጡት ለፈጠራቸው ሰዎች የሚበጀውን ከማንም በላይ ከሚያውቀው አላህ የሚያውቁ አይደሉም::

{أَلَا يَعۡلَمُ مَنۡ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلۡخَبِيرُ ﴿١٤﴾}[الملك: ١٤]

‹‹የፈጠረ አምላክ እርሱ ዕውቀተ ረቂቁ፣ውስጥ አዋቂው ሲኾን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን::››[አል ሙልክ:14]

አለዚያማ አሻሻዩና ለዋዋጩ ራሱን ለፈጠራቸው ሰዎች የሚበጀውን ከማንም በላይ የሚያውቅ ፈጣሪ ጌታ አድርጎ ሾሟል ማለት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ግን ይህን ከመፍቀድ የጠራና ላቀ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَغَيۡرَ دِينِ ٱللَّهِ يَبۡغُونَ وَلَهُۥٓ أَسۡلَمَ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ طَوۡعٗا وَكَرۡهٗا وَإِلَيۡهِ يُرۡجَعُونَ ﴿٨٣﴾}[آل

https://www.path-2-happiness.com/am
https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

[عمران: ٨٣]

‹‹በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ፤በውድም በግድም ለርሱ የታዘዙ፣ወደርሱም የሚመለሱ ሲኾኖ (ከሓዲዎች) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን?››[ኣሊ ዒምራን:83]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيْنَهُمْ} [النساء: ٦٥]

‹‹በጌታህም እምላለሁ (አላህ በራሱ መማሉ ነው) በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከሚያስፈርዱህ፣ . . ድረስ አያምኑም፤(ምእመን አይኾኑም)::››[አል ኒሳእ:65]

ሁለተኛ፦ ሃማኖቱ አንድ አላህን ብቻ ለመገዛትና እርሱን ብቻ ለማምለክ ጥሪ የሚያደርግ፣በርሱ ማጋራትን (ሽርክን) የሚከለክል መሆን:: ለተውሒድ ጥሪ ማድረግ የሁሉም ነብያትና መልክተኞች ጥሪ መሠረት ነው:: ሽርክ፣ባእድ አምልኮና ጣዖታዊነት ደግሞ ከጤናማ ተፈጥሮና ከአስተዋይ አእምሮ ሀሁ ጋር የሚጣረስ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِىٓ إِلَيْهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعْبُدُونِ ﴿٢٥﴾} [الأنبياء: ٢٥]


‹‹ከአንተ በፊትም፣እነሆ ከኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢኾን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም::››[አል አንቢያ:25]

እያንዳንዱ ነብም ለሕዝቦቹ እንዲህ ብሏል፦

{ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ إِنِّىٓ أَخَافُ عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿٥٩﴾} [الأعراف: ٥٩]

‹‹አላህን ተገዙ፤ለናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም፤እኔ በናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁ::››[አል አዕራፍ:59]

በመሆኑም ሽርክን የሚቀበል፣ነብይንም ይሁን መልኣክን ወይም ጻድቅን (ወሊይ)፣ሰብአዊ ፍጡርንም ይሁን ግኡዝ ነገርን በአላህ አምልኮ የሚያጋራ ማንኛውም ሃይማኖት ተቀባይነት




## የአላህ ፍጡር

‹‹በዚህ ዓለም ላይ ያለው እያንዳንዱ ነገር በሆነ ምክንያት የተፈጠረ አድርገው ስለሚቆጥሩ፣ትናንሽ ሕጻናት በአምላክ የማመን ቀዳሚ ተፈጥሮያዊ ዝግጅት አላቸው:: ይህም ብቻ ሳይሆን ሕጻናት ወደ አንዱ ደሴት ወስደን ብንጥላቸውና ለብቻቸው ቢያድጉ በአላህ የሚያምኑ ሆናሉ::››

ጃስቶን ባሪየት

በኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ የሰብአዊ ሳይንስ ተመራማሪ



## የአፈተረት ደዌ

‹‹ሳይንስ ለአፈተረቶች መርዝ መድኃኒት ነው››

አዳም እስሚዝ

እስኮትላንዳዊ ፈላስፋ

የሌለው ውድቅ ሃይማኖት ነው:: አምልኮ (ዕባዳ) ተጋሪ ለሌለው ለአንድ አላህ ብቻ የተገባ ሲሆን፣ሽርክና ጣዖታዊነት ግልጽ ጥመት ነው:: መሰረቱ ከአላህ ዘንድ ቢሆን እንኳ ሽርክ ብክለት የገባባት ማንኛውም ሃይማኖትም ውድቅና ተቀባይነት የሌለው ሃይማኖት ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) ለዚህ አስደናቂ ምሳሌ ሲገልጽልን እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٌ فَٱسْتَمِعُوا۟ لَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخْلُقُوا۟ ذُبَابًا وَلَوِ ٱجْتَمَعُوا۟ لَهُۥ ۖ وَإِن يَسْلُبْهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيْـًٔا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ ٱلطَّالِبُ وَٱلْمَطْلُوبُ ﴿٧٣﴾ مَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦٓ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَقَوِىٌّ عَزِيزٌ ﴿٧٤﴾} [الحج: ٧٣- ٧٤]

‹‹እላንተ ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለጸላችሁ፤ለርሱም አድምጡት፤እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገግዟቸው (ጣዖታት)፣ዝምብን ፈጽሞ አይፈጥሩም፤ለርሱ (ለመፍጠር)፣ቢሰበሰቡም እንኳ፣(አይችሉም)፤አንዳችንም ነገር ዝንቡ ቢነጥቃቸው ከርሱ አያስጥሉትም፤ፈላጊውም ተፈላፊውም ደከሙ (ገዥውም ተገዥውም ደካሞች ናቸው):: አላህን ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም፤አላህ በጣም ኃያል አሸናፊ ነው::››[አል ሐጅ:7374]

ሦስተኛ፦ ከሰው ልጅ ትክክለኛና ጤናማ ተፈጥሮ ጋር የሚጣጣም መሆን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًا ۚ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَا ۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ ٱللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾} [الروم: ٣٠]

‹‹ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያውቁም::››[አል ሩም:30]

ተፈጥሮ የሰዎች ፈጣሪ ሰዎችን የሕልውናቸው አካል አድርጎ የፈጠራባቸውን ሁሉ የሚያካትት ሲሆን፣ሃይማኖት ከሰው ልጅ ተፈጥሮ ጋር የማይጣጣም ሊሆን አይችልም:: አለዚያ ፈጣሪ ሃይማኖቱን አልደነገገም ማለት ሲሆን ይህ ደግሞ ሊሆን የማይችልና ሽርክም ነው::

አራተኛ፦ ከትክክለኛ አእምሮ ጋር የጠጣጣመ መሆን:: ይህም ትክክለኛ ሃይማኖት የአላህ ሕግ፣ትክክለኛ አእምሮም የአላህ ፍጡር በመሆናቸው የአላህ ሕግ ከአላህ ፍጡር ጋር ፈጥሞ ሊጣረስ አይችልም:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ

https://www.path-2-happiness.com/am

ብሏል፦

{أَفَلَمۡ يَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَتَكُونَ لَهُمۡ قُلُوبٞ يَعۡقِلُونَ بِهَآ أَوۡ ءَاذَانٞ يَسۡمَعُونَ بِهَاۖ فَإِنَّهَا لَا تَعۡمَى ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَلَٰكِن تَعۡمَى ٱلۡقُلُوبُ ٱلَّتِي فِي ٱلصُّدُورِ ٤٦}[الحج: ٤٦]

‹‹ለነርሱም፣በነርሱ የሚያውቁባቸው ልቦች፣ወይም በነርሱ የሚሰሙባቸው ጆሮዎች፣ይኖሩዋቸው ዘንድ፣በምድር ላይ አይኼዱምን? እነሆ ዓይኖች አይታወሩም ግን እነዚያ በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ይታወራሉ::››[አል ሐጅ:46]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ٣ وَفِي خَلۡقِكُمۡ وَمَا يَبُثُّ مِن دَآبَّةٍ ءَايَٰتٞ لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ٤ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن رِّزۡقٖ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَا وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ ءَايَٰتٞ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ٥ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ نَتۡلُوهَا عَلَيۡكَ بِٱلۡحَقِّۖ فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَ ٱللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ يُؤۡمِنُونَ ٦}[الجاثية: ٣ـ ٦]

‹‹በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምእመናን ሁሉ (ለችሎታው) እርግጠኛ ምልክቶች አሉ:: እናንተንም በመፍጠር፣ከተንቀሳቃሽም (በምድር ላይ) የሚበትነውን ሁሉ (በመፍጠሩ) ለሚያረጋግጡ ሕዝቦች ታምራቶች አሉ:: በሌሊትና መዓልት መተካካትም፣ከሲሳም (ከዝናም) አላህ ከሰማይ ባወረደው፣በርሱም ምድርን ከሞተች በኋላሕያው በማድረጉ፣ነፋሶችንም (በያቅጣጫቸው) በማዘዋወሩ፣ለሚያውቁ ሕዝቦች ማስረጃዎች አሉ:: እነዚህ፣ ባንተ ላይ የምናነባቸው ሲኾኑ፣የአላህ ማስረጃዎች ናቸው፣ከአላህና ከማስረጃዎቹም ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ?››[አል ጃሢያ:3-6]

እውነተኛ ሃይማኖት በአፈተረረት፣በቅዠት ሀሳቦችም ሆነ አንዱ ሌላውን በሚጻረር ሁኔታ በቅራኔዎች



## ማስረጃችሁን አምጡ

‹‹ጥበበኛ ሰው እምነቱን በማስረጃ ላይ የሚያነጽ ነው››

ዴቪድ ሂዩም
እስኮትላንዳዊ ፈላስፋ

## የሰው ሰውነት በስነምግባሩ ነው

‹‹ስነምግባር የሌለው ሰው በዓለም ተፈቶ የተለቀቀ አውሬ ነው››



አልቤር ካሞ
ፈረንሳዊ ፈላስፋ



የተሞላ ሊሆን አይችልም:: ይህ ከጤናማ አመዛዛኝ አእምሮ ጋር የሚጻረር ነው:: አንድን ትእዛዝ አስተላልፎ በሌላ ትእዛዝ ደግሞ ተቃራኒውን አያዝም:: ለአንዱ ቡድን አንድን ነገር ፈቅዶ ለሌላው ቡድን ያንኑ ነገር እርም አያደርግም፤በተመሳሳይ ጉዳዮች ላይ የተለያየ ብያኔ አይሰጥም እርስ በርሳቸው የሚጣረሱ ውሳኔዎችን አያስተላልፍም::

አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلۡقُرۡءَانَۚ وَلَوۡ كَانَ مِنۡ عِندِ غَيۡرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ ٱخۡتِلَٰفٗا كَثِيرٗا ٨٢}[النساء: ٨٢]

‹‹ቁርኣንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር::››[አል ኒሳእ:82]

ይልቁንም በግልጽ ማስረጃዎች ላይ የተመሰረተ መሆኑም የግድ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦


{قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١١١}[البقرة: ١١١]

‹‹እውነተኞች እንደኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ፣በላቸው::››[አል በቀራህ:111]

አምስተኛ፦ ለሰመልካም ስነምግባርና ለሰናይ ተግባራት ጥሪ የሚያደርግ መሆን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ١٥١ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۖ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ لَا نُكَلِّفُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۖ وَإِذَا قُلۡتُمۡ فَٱعۡدِلُواْ وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰۖ وَبِعَهۡدِ ٱللَّهِ أَوۡفُواْۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ١٥٢ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسۡتَقِيمٗا فَٱتَّبِعُوهُۖ وَلَا

www.path-2-happiness.com




## ተጨባጭ ሁን

‹‹ሕይወትን ተጨባጭ በሆነ ሁኔታ መመልከቱ፣ፍጹማዊ ልባዊ ምክሩ፣ለደግነትና ለመተዛዘን ጥሪ ማድረጉ፣ጥልቅ የሆነው የሰው ልጅ ትሩፋታዊ ተፈጥሮ መያዙ፣እነዚህና ሌሎቹም ምክንያቶች የእስላም ሃይማኖት አውነተኛ ስለመሆኑ ለኔ ከሁሉም የላቀ ታላቅ ማስረጃ ነበሩ::››

ዮል

ዴንማርካዊ ኦሪየንታሊስት



## ስነምግባር እፎይታ ነው

‹‹እኔ የማውቀው ስነምግባራዊ የሆነ ተግባር ከፈጸምከው በኋላ እፎይታ የሚሰጥህ መሆኑንና ኢስነምግባራዊ የሆነው ደግሞ ከፈጸምከው በኋላ እርካታ የማይሰጥህ መሆኑን ነው ነው::››

አርነስት ሀሚንግዌይ

አሜሪካዊ ጸሐፊ

https://www.path-2-happiness.com/am

تَتَّبِعُواْ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمْ عَن سَبِيلِهِۦۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٥٣﴾}[الأنعام: ١٥١-١٥٣]

‹‹፦ ኑ፤ጌታችሁ በናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በርሱም ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ በላቸው፤በርሱ (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ፤ለወላጆችም በጎን ሥራ (ሥሩ)፤ልጆቻችሁንም ከድኽነት ፍራቻ አትግደሉ፤እኛእናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና፤መጥፎ በሥራዎችንም ከርሷ የተገለጸውንም የረደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ፤ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢኾን እንጅ አትግደሉ፤ይሃችሁ ታውቁ ዘንድ (አላህ) በርሱ አዘዛችሁ:: የየቲምንም ገንዘብ፣ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኹኔታ እንጂ አትቅረቡ፤ስፍርንና ሚዛንንም በትክክል ምሉ፤ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም፤በተናጋራችሁም ጊዜ፣ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢኾንም እንኳ፣ (እውነትን በመናገር) አስተካክሉ፤በአላህም ቃል ኪዳን ምሉ፤ ይኻችሁ ትገሠጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ:: ይህም ቀጥተኛ ሲኾን መንገዴ ነው፤ ተከተሉትም፤(የጥመት) መንገዶችንም አትከተሉ፤ከ(ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይለያዩዋችኋልና:: ይኻችሁ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ::››[አል አንዓም፡151-153]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَٱلۡإِحۡسَٰنِ وَإِيتَآيِٕ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَيَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِ وَٱلۡبَغۡيِۚ يَعِظُكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ﴿٩٠﴾}[النحل: ٩٠]

‹‹አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፤ ከአስከፊም፣ (ከማመንዘር)፣ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፤ትገነዘቡ ዘንድ፣ ይገሥጻችኋል::››[አል ነሕል፡90]

ለውሸት፣ለግድያ፣ለግፍ፣ለበደል፣ ለስርቆት፣አስገድዶ ለመድፈር፣ወላጆችን ለማስከፋትም ሆነ ለመሳሰሉት እኩይ ነገሮች ጥሪ የሚያደርግ ሃይማኖት ትክክለኛ ሃይማኖት ሊሆን አይችልም::

ስድስተኛ፦ የሰው ልጅ ከፈጣሪው ጋር የሚኖረውን ግንኙነትና ሰብአዊ ፍጡራን እርስ በርሳቸው በመካከላቸው የሚኖረውን ትስስር የሚያደራጅ መሆን:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ أَسۡمَآءٗ سَمَّيۡتُمُوهَآ أَنتُمۡ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن سُلۡطَٰنٍۚ إِنِ ٱلۡحُكۡمُ إِلَّا لِلَّهِ أَمَرَ أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٤٠﴾}[يوسف: ٤٠]

‹‹ከርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትግገዙም፤አላህ በርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም፤ፍርዱ የአላህ እንጅ የሌላ አይደለም፤እርሱን እንጅ ሌላን እንዳትግገዙ አዟል፤ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም::››[ዩሱፍ ፡40]

ያ ሃይማኖት የሰው ልጅ ፈጣሪውን አስመልክቶ የሚኖሩበትን ግዴታዎች ማደራጀት፣በሰዎች መካከል የሚኖሩትን ግንኙነቶችም ሥርዓት የሚያስይዝ መሆን ይኖርበታል:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗا وَبِذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱلۡجَارِ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡجَارِ ٱلۡجُنُبِ وَٱلصَّاحِبِ بِٱلۡجَنۢبِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِ وَمَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡ}[النساء: ٣٦]

‹‹አላህንም ተገዙ፤በርሱም ምንንም አታጋሩ፣በወላጆችና በቅርብ ዝምድና ባለቤትም፣ በየቲሞችም፣ በምስኪኖችም፣



## ምርጡ ውርስ

ነገሮች ዋነኛው ሸሪዓ በመባል የሚታወቀው ሃይማኖታዊ ሕጉ ነው:: የእስላም ሸሪዓ በዓይነቱ ልዩ ሲሆን፣የያንዳንዱን ሙስሊም ሕይወት በሁሉም ፈርጅ የሚያደራጅ የመለኮታዊ ትእዛዛት ስብስብ ነው:: አምልኮንና ሃይማኖታዊ ስነ ሥርዓቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን ፖለቲካዊና ሕጋዊ መርሆዎችን ያካትታል::››

ጆዜፍ ሻኽት

ጀርመናዊ ኦሪየንታሊስት

https://www.path-2-happiness.com/am

በቅርብ ጎረቤትም፣በሩቅ ጎረቤትም፣በጎን ባልደረባም፣ በመንገደኛም፣ እጆቻችሁም ንብረት ባደረጓቸው (ባሮች)፣መልካምን (ሥሩ)፤አላህ ኩራተኛ ጉረኛ የኾነን ሰው አይወድም::››[አል ኒሳእ:36]

ሰባተኛ፦ ለሰብአዊ ፍጡር ከበሬታ የሚሰጥና በተከታዮቹ መካከል በጾታ፣በቆዳ ቀለምም ሆነ በዘር ምክንያት ምንም ዓይነት አድልዖ የማያደርግ መሆን:: የሰዎች መበላለጫ ብቸኛው መለኪያ አላህን በመፍራትና በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ሰናይ ተግባሩ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَقَدۡ كَرَّمۡنَا بَنِيٓ ءَادَمَ وَحَمَلۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ}[الإسراء: ٧٠]

‹‹የኣደምንም ልጆች በእርግጥ (ከሌላው ፍጡር) አከበርናቸው፤በየብስና በባሕርም አሳፈርናቸው፤››[አል እስራእ:70]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ﴿١٣﴾}[الحُجُرات: ١٣]

‹‹እላንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤እንድትተዋወቁም ጎሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤አላህ ግልጽን ዐዋቂ፣ውስጥንም ዐዋቂ ነው::››[አል ሑጁራት:13]

ስምንተኛ፦ ምንም ዓይነት ወለም ዘለም ወደሌለበት፣ለሰዎች መድህን ወዳለበት፣መሪ ብርሃን ወደሚሆናቸው ቀጥተኛው መንገድ የሚመራ መሆን:: ጋኔን (ጅንን) ቁርኣንን አዳምጦ እርስ በርሳቸው የተባባሉትን ሲነግረን አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قَالُواْ يَٰقَوۡمَنَآ إِنَّا سَمِعۡنَا كِتَٰبًا أُنزِلَ مِنۢ بَعۡدِ مُوسَىٰ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِ يَهۡدِيٓ إِلَى ٱلۡحَقِّ وَإِلَىٰ طَرِيقٖ مُّسۡتَقِيمٖ ﴿٣٠﴾}[الأحقاف: ٣٠]

‹‹አሉም ፦ ሕዝቦቻችን ሆይ! እኛ ከሙሳ በኋላ የተወረደን መጽሐፍ፣በፊቱ ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥ፣ወደ እውነትና ወደ ቀጥተኛ መንገድ የሚመራ የኾነን ሰማን::››[አል አሕቃፍ:30]

በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلۡقُرۡءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٞ وَرَحۡمَةٞ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ وَلَا يَزِيدُ



ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا خَسَارٗا ﴿٨٢﴾}[الإسراء: ٨٢]

‹‹ከቁርኣንም፣ለምእመናን መድኅኒትና እዝነት የኾነን እናወርዳለን፤በዳዮችንም ከሳራን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም::››[አል እስራእ: 82]

ቁርኣን ከማይምነትና ከጥመት ጨለማ ወደ አላህ ተገዥነትና የሁለቱም ዓለማት ተድላ ሰዎችን የሚወስድ መሪ ብርሃን ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ قَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمۡ كَثِيرٗا مِّمَّا كُنتُمۡ تُخۡفُونَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَعۡفُواْ عَن كَثِيرٖۚ قَدۡ جَآءَكُم مِّنَ ٱللَّهِ نُورٞ وَكِتَٰبٞ مُّبِينٞ ﴿١٥﴾}[المائدة:١٥]

‹‹የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! ከመጽሐፉ ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልጽ፣ከብዙውም የሚተው ሲኾን መልክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ:: ከአላህ ዘንድ ብርሃንና ገላጭ መጽሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ::››[አል ማእዳህ:15]


በተጨማሪም አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَآ إِكۡرَاهَ فِي ٱلدِّينِۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشۡدُ مِنَ ٱلۡغَيِّۚ فَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسۡتَمۡسَكَ بِٱلۡعُرۡوَةِ ٱلۡوُثۡقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَاۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٢٥٦﴾ ٱللَّهُ وَلِيُّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يُخۡرِجُهُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَوۡلِيَآؤُهُمُ ٱلطَّٰغُوتُ يُخۡرِجُونَهُم مِّنَ ٱلنُّورِ إِلَى ٱلظُّلُمَٰتِۗ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٢٥٧﴾}
[البقرة: ٢٥٦- ٢٥٧]

‹‹በሃማኖት ማስገደድ የለም፤ቅኑ መንገድከጠማማው በእርግጥ ተገለጠ፤በጣዖትም የሚክድና በአላህ

https://www.path-2-happiness.com/am

የሚያምን ሰው፣ለርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ፤አላህም ሰሚ ዐዋቂ ነው። አላህ የእነዚያ ያመኑት ሰዎች ረዳት ነው፤ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል፤እነዚያም የካዱት ረዳቶቻቸው ጣዖታት ናቸው፤ከብርሃን ወደ ጨለማዎች ያወጧቸዋል፤እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፤እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።››[አል በቀራህ:256-257]



### እኩልነት አልባ

‹‹ከእኩልነት መልኮች አስከፊው እኩል ያልሆኑ ነገሮችን እኩል ለማድረግ መሞከር ነው።››

አርስቶትል

ግሪካዊ ፈላስፋ



### በአላህ ታገዝ

‹‹ያለ ረዳትና ያለ ደጋፊ ብቻቸውን የሕይወትን ፍልሚያ ከሚጋፈጡ፣ መለኮታዊ ረድኤት እገዛን ቢለምኑ ኖሮ ምናልባት ካሁኗ አፍታ ጀምሮ በአእምሮ ሕሙማን ሆስፒታሎች ውስጥ በመጪጪህ ላይ የሚገኙ በሺዎች የሚቆጠሩ ተሰቃዮችን ማደን ይቻል ይሆናል።››

ዴል ካርኒጀ
አሜሪካዊ ደራሲ



## የሚያስፈልገን ሃይማኖት የቱ ነው?!

ከላይ የተዘረዘሩ የእውነተኛው ሃይማኖት መመዘኛዎችን የሚሏው ሃይማኖት የትኛው ነው?!

በምንጫው መሠረት ሃይማኖቶችን በሁለት መደብ መክፈል ይቻላል፦

ሰዎች የሚወስኗቸና የሚያሻሽሏቸው፣ከአላህ (ሱ.ወ.) ያልተላለፉ መለኮታዊ ያልሆኑ ምድራዊ ሰው ሠራሽ ሃይማኖቶች። እነዚህ እንደ ቡድሂዝም ሐሕንዱ ዞሪስቴሪያንና ጣዖታዊነት ያሉ እምነቶች ሲሆኑ፣አምነታቸው ከግላዊ ዝንባሌዎቻቸው የሚመነጭና ከእውነተኛው ሃይማኖት ፈጽሞ የራቀ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٢٣﴾}[الجاثية: ٢٣]

‹‹ዝንባሌውን አምላኩ አድርጎ የያዘውን፣አላህም ከዕውቀት ጋር ያጠመመውን፣በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን፣በዓይኑም ላይ ሽፋን ያደረገበትን ሰው አየህን! ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማነው? አትገሠጹምን?››[አል ጃሢያ:23]

እንዲህ ዓይነቱ እምነት የሰው ልጅ ስሜታዊ ዝንባሌ የፈጠረው እንጂ ፈጽሞ መለኮታዊ ሃይማኖት አይደለም። ሰው ሠራሽ ሃይማኖቶች በአፈ-ተረቶች፣በቅዠት ሀሳቦች፣በመደብ በደልና ጭቆና እና በቅራኔዎች የታጨቁ ናቸው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُوا۟ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴿٨٢﴾}
[النساء: ٨٢]

‹‹ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ



### አላህ ግን አንድ ነው

‹‹በምድራዊ ሃይማኖቶች ውስጥ ያሉትን አማልክት ብዛት መቁጠር ለተመራማሪዎች አድካሚ ሆኗል። የጥንት ግብጻውያን አማልክት ቁጥር ከ800 በላይ ነው። የሂንዱዎች አማልክት ብዛት ከ10000 በላይ ነው። በግሪኮች በቡድሂስቶችና በተቀሩት የምድራዊ ሃይማኖቶች ተከታዮች ዘንድም ይህንኑ ዓይነት ጣዖታዊነት እናስተውላለን።››

https://www.path-2-happiness.com/am



ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር።››[አል ኒሳእ፡82]

ከአላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ የተላለፉ እንደ አይሁዳዊነት ክርስትና እና እስላም ያሉ መለኮታዊ ሃይማኖቶች። ለነዚህ ሃይማኖቶች ተከታዮች ፈጣሪ አምላክ ሃይማኖታቸውን ደንግጎላቸው መርጦላቸዋል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحًا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِۚ كَبُرَ عَلَى ٱلۡمُشۡرِكِينَ مَا تَدۡعُوهُمۡ إِلَيۡهِۚ ٱللَّهُ يَجۡتَبِيٓ إِلَيۡهِ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِيٓ إِلَيۡهِ مَن يُنِيبُ ١٣}[الشورى: ١٣]

‹‹ለናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑሕን ያዘዘበትን ደነገገላችሁ፤ያንንም ወደ አንተ ያወረድነውን፣ያንንም በርሱ ኢብራሂምን፣ሙሳንና ዒሳንም ያዘዝንበትን፣ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ፣በርሱም አትለያዩ፣ማለትን (ደነገግን) በአጋሪዎቹ ላይ ያ ወደርሱ የምትጠራቸው ነገር ከበዳቸው፤አላህ የሚሻውን ሰው ወደርሱ (እምነት) ይመርጣል፤የሚመለስንም ሰው ወደርሱ ይመራል።››[አል ሹራ፡13]



## እውነተኛው ሕግ

‹‹ገብቶኛል . . . ተረድቼአለሁ . . ለሰው ልጅ አስፈላጊው ነገር እውነትን የሚያረጋግጥ፣ሐሰትን የሚያስወግድ መለኮታዊ ሕግ ነው።››

ቶሊስቶይ

ሩሲያዊ የስነጽሑፍ ሰው

ሰው ሠራሽ ምድራዊ ሃይማኖቶች ከደንጋጊዎቻቸው ስሜታዊ ዝንባሌዎች ጋር የሚጣጣሙና ከአጭር ጊዜ በኋላ ሰዎች አይረቤነታቸውን በመረዳት በየጊዜው ለማሻሳልና ለመለዋወጥ የሚሞክሯቸውን ዝርዝር ሀሳቦችና አቋሞችን ያካተተ ግዙፍ ስብስብ መሆናቸው ጥርጥር የለውም። እነዚህ ምድራዊ ሕጎች ካሏቸው በርካታ መለያ ባሕርያት መካከል የሚከተሉትን እናገኛለን፦

በአላህ ማጋራት (ሽርክ) ፦ በየዕለቱ የሚያመልኩባቸውን አዳዲስ አማልክት ያመርታሉ፤አማልክቶቻቸው የራሳቸው እጅ ሥራ ውጤቶች ናቸው። ከኃያሉ አላህ ጋር ባእድ አማልክት ፈጽሞ መኖር እንደማይችሉ አያስተውሉም ወይም አያስተነትኑም። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{مَا ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ مِن وَلَدٖ وَمَا كَانَ مَعَهُۥ مِنۡ إِلَٰهٍۚ إِذٗا لَّذَهَبَ كُلُّ إِلَٰهِۭ بِمَا خَلَقَ وَلَعَلَا بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ ٩١ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٩٢}[المؤمنون: ٩١ - ٩٢]

‹‹አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፤ከርሱም ጋር አንድም አምላክ የለም፤ያን ጊዜ፣(ሌላ አምላክ በነበረ)፣አምላክ ሁሉ በፈጠረው ነገር በተለየ ነበር፤ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በላቀ ነበር፤አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ። ሩቁንና ቅርቡንም ሁሉ ዐዋቂ ነው፤(በርሱ) ከሚያጋሩትም ሁሉ ከፍ አለ።››[አል ሙእሚኑን፡ 91-92]

ማሕበራዊ የመደብ ጭቆና ፦ መለኮታዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ደንጋጊዎቹ ለራሳቸው፣ ለቡድናቸው መደብና ለሚፈልጓቸው መደቦች ከሌሎች የተለየ ልዩ መብቶች ይሰጧቸዋል። ይህም ፍላጎታቸውን ለማርካትና ሌሎችን የነሱ መብት አልባ አገልጋዮች ለማድረግ ዓላማ ነው። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن ذَكَرٖ وَأُنثَىٰ وَجَعَلۡنَٰكُمۡ شُعُوبٗا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓاْۚ إِنَّ أَكۡرَمَكُمۡ عِندَ ٱللَّهِ أَتۡقَىٰكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٞ ١٣}[الحجرات: ١٣]

‹‹እላንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ፤እንድትተዋወቁም ጎሣዎችና ነገዶች አደረግናችሁ፤አላህ ዘንድ በላጫችሁ፣በጣም አላህን ፈሪያችሁ ነው፤አላህ ግልጽን ዐዋቂ፣ውስጥንም ዐዋቂ ነው።››[አል ሑጁራት፡13]

አላህ (ሱ.ወ.) ሌሎችን በንቀት ዓይን መመልከትንና በማንም ቢሆን መሳለቅን ከልክሏል። አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{لَا يَسۡخَرۡ قَوۡمٞ مِّن قَوۡمٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُونُواْ خَيۡرٗا مِّنۡهُمۡ}[الحجرات: ١١]

‹‹ወንዶች ከወንዶች አይቀልዱ፤ከነርሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤ሴቶችም ከሴቶች (አይሳለቁ)፤ከነሱ የበለጡ ሊኾኑ ይከጀላልና፤››[አል ሑጁራት፡11]

ስለዚህም አላህ (ሱ.ወ.) ዘንድ ነጩ በጥቁሩ ላይ፣አንዱ ጎሳ በሌላው ጎሳ ላይ፣አንዱ ሕዝብ በሌላው ሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት ብልጫ የለውም። በተቃራኒው ግን ከነዚህ ምድራዊ ሃይማኖቶች ብዙዎቹ በአስከፊ የመደብ አድልዖና ጭቆና ላይ የታነጹ ናቸው።



## ግፈኛው የመደብ ክፍፍል

‹‹የሕንዱ መደባዊ ክፍፍል እንዲከተለው የተደለደለ ነው፦ የነጮች መደብ፣ይህ የሃይማኖት መሪዎችንና አዋቂዎችን የያዘ ነው። የቀያዮች መደብ፣ይህ ደግሞ መሳፍንቱንና ፈረሰኞችን ያቀፈ ነው።የብጫዎች መደብ፣ይህ ገበሬዎችንንና ነጋዴዎችን ያቀፈ ነው። የጠቋቁሮች መደብ፣ ይህ ደግሞ የሞያና የእደጥበብ ሠራተኞችን ያጠቃለለ ነው። አምስተናው መደብ ወይም የእርኩሳን መደብ በመባል የሚታወቀው ደግሞ በተቀሩት የተናቁ ሥራዎች ላይ የተሰማሩትን ሁሉ ያካትታል። የላይኞቹ መደቦች በታችኞቹ መደቦች ላይ የጌትነት ሥልጣን ሲኖራቸው፣የታችኞቹ መደቦች ደግሞ ለላይኞቹ መደቦች አገልጋይ የመሆን ግዴታ አለባቸው።››

https://www.path-2-happiness.com/am

https://www.path-2-happiness.com/am

የሰውን ተፈትሮ መጻረር ፦ ምድራዊ ሰው ሠራሽ ሃይማኖቶች የሰውን ተፈጥሮ በመጻረር የማይችለውንና የማገባውን በማሸከም ላይ የተመሰረቱ፣ሰብአዊ ተፈጥሮንና ጤናማ አእምሮን በመቃረን የቆሙ፣ተከታዮቻቸው ከቀጥተኛው መንገድ ርቀው ያፈነገጡ ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{فَأَقِمۡ وَجۡهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفٗاۚ فِطۡرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيۡهَاۚ لَا تَبۡدِيلَ لِخَلۡقِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ۝٣٠}[الروم: ٣٠]

‹‹ወደ እውነት ተዘንባይ ኾነህ ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ፤የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃማኖት ያዙዋት)፤የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም፤ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው፤ግን አብዛኞዎቹ ሰዎች አያውቁም::››[አል ሩም:30]

አፈተረቶችና የቅዠት ሀሳቦች ፦ እነዚህ ምንም ዓይነት አእምሯዊ ሎጂካዊም ሆነ ሳይንሳዊ መነሻ ሳይኖራቸው በባዶ ቅዠት ላይ የተመሰረቱ እምነቶች ወይም አስተሳሰቦች ናቸው:: ምድራዊ ሃይማኖቶች አንዳች ማስረጃም ሆነ መሰረት በሌላቸው ተራ የቅዠት ሀሳቦች የተሞሉ ሲሆን በቅዠት ላ ሊመሰረት የሚችለው ቅዠት ብቻ ነው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ۝٦٤}[النمل: ٦٤]

‹‹እውነተኞች እንደኾናችሁ አስረጃችሁን አምጡ፣በላቸው::››[አል ነምል:64]

እርስ በርሳቸው መጣረስ ፦ ሰው ሠራሽ እምነቶች በቅራኔዎች የተሞሉ፣እያንዳንዱ ቡድን ከተቃረነውና ከአብራኩ ወጥቶ በተሸሻለው ሌላው ቡድን ውድመትና ፍርስራሽ ላይ የተመሰረቱ ናቸው:: አላህ (ሱ.ወ.) እንዲህ ብሏል፦

{وَلَوۡ كَانَ مِنۡ عِندِ غَيۡرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ ٱخۡتِلَٰفٗا كَثِيرٗا ۝٨٢}[النساء: ٨٢]

‹‹ከአላህ ሌላ ዘንድ በነበረ ኖሮ፣በርሱ ውስጥ ብዙን መለያየት ባገኙ ነበር::››[አል ኒሳእ:82]

መለኮታዊ ሃይማኖቶች ግን፣የአላህን ቃልና መልክቱን ያደርሱ ዘንድ መልክተኞችን በመላክ ሲመራቸውና መንገዱን ሲያበራላቸው፣ከከንቱነትና ከመዋለል፣ከአፈተረትና ከማጋራት፣የሰውን ተፈጥሮና ሰብአዊ አእምሮን ከመጻረር ሲያርቃቸው ከአላህ ለሰው ልጆች የተቸሩ ጸጋዎቹ ናቸው::

{رُّسُلٗا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى ٱللَّهِ حُجَّةُۢ بَعۡدَ ٱلرُّسُلِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمٗا ۝١٦٥}[النساء: ١٦٥]

‹‹ከመልክተኞቹበኋላለሰዎችበአላህላይአስረጅእንዳይኖር፣አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች የኾኑን መልክተኞች (ላክን)፤አላህም አሸናፊ ጥበበኛ ነው::››[አል ኒሳእ:165]





## የቡድሂዝም መጣረስ

‹‹ቡድሂስቶች ወይም ከፊሎቻቸው የአምላክን መኖር ሲያስተባብሉ፣ቡድሃን የአምላክ ልጅ ነው ይላሉ:: መንፈስ መኖሩንም ሲያስተባብሉ የሙታን ነፍስ በሌላ ፍጡር አካል ትመለሳለች ብለው ያምናሉ:: ››